# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሲፒርየር ፍርድ ቤት
## የወንጀለኛ ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን)
## የፍርድ ቤት ቅረቡ መጥሪያ ማስታወቂያ (ኖቲስ ቲ አፒር ኢን ኮርት) ወይም ተመላሽ የማይደረግ ገንዘብ ከፍሎ መለቀቅ (ፖስት ኤንድ ፎርፈይቸር)

*የአውራ ጣት አሻራ (ታምብ ፕሪንት)*

| **የእስረኛ መረጃ (ሳብጀክት ኢንፎርሜሽን)** | | | |
|---|---|---|---|
| የእስር ቁጥር (አረስት ናምበር) | ሲ.ሲ.ኤን. | ፒ.ዲ.አይ.ዲ. | የልደት ቀን |
| የጣቢያ ጸሀፊ (ስቴሽን ክለርክ)/ኦፊሰር/ባጅ/ዩኒት/ካድ. ቁጥር | | የጥፋት (ኦፈንስ) ፒ.ኤስ.ኤ. | |
| የታሳሪ ስም፡ **መጨረሻ፣ መጀመሪያ፣ መሀከለኛ** | | | |

**በሚከተሉት ጥፋት(ቶች) ምክኒያት ቁጥጥር ስር ውስጥ ገብተዋል**
*[እባክዎ ሁሉንም በቁጥጥር ስር ውስጥ እንዲገቢ ያደረጉ ክሶች ይዘርዝሩ]*

## መለቀቂያና ወደ ፍርድ ቤት መመለሻ መረጃ (ረሊዝ ኤንድ ሪተርን ቱ ኮርት ኢንፎርሜሽን)

### ☐ ሳይታሰሩ መለቀቅ ብቻ (ሳይቴሽን ረሊዝ ኦንሊ)

*ኦፊሰሮች፡ እባክዎ ተገቢ በሆነ የፍርድ ቤት ቦታ ምልክት ያድርጉና በፍርድ ቤቱ ድረገጽ ባለው የቀን ቻርት በመጠቀም ቀን ይምረጡ።*

ከታች በተቀመጠው **ቀንና ሰአት** በ500 Indiana Ave., NW, Washington, D.C. በሚገኘው የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሱፒርየር ፍርድ ቤት እቀርባለው በማለት በሰጡት ቃል መሰረት ነው ፍርድ ቤቱ እየለቀቅዎ ያለው፡

☐ **የኦ.ኤ.ጂ. ክስ(ሶች) ብቻ**

______________________ በ ______9:30 ኤ.ኤም. __
**ቀን** **ሰአት**
**በፍርድ ቤት ቁጥር C-10**

☐ **የዩ.ኤስ. ክስ(ሶች) ብቻ**

________________________ በ 10፡00 ኤ.ኤም. በፍርድ ቤት ቁጥር C-10
**ቀን** **ሰአት**

☐ **የዩ.ኤስ. እና ኦ.ኤ.ጂ. ክሶች**

________________________ በ 10፡00 ኤ.ኤም. በፍርድ ቤት ቁጥር C-10
**ቀን** **ሰአት**

ይህ ፍርድ ቤት ቅረብ የሚል ማስታወቂያ (ኖቲስ ቱ አፒር) መቀበሌ አረጋግጣለሁ። ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰአት እንደምቀርብ ቃል እገባለሁ። ሳልቀርብ ብቀር እንድታሰር የሚያደርግ የፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ (ቤንች ዋራንት) ሊተላለፍብኝ እንደሚችል እገነዘባለሁ። በተጨማሪ ፍርድ ቤት ሳልቀርብ ብቀር በወንጀል ጥፋት ተከስሼ ፍርድ ቤት ባለመቅረብ ወንጀለኛ ነህ የሚል ፍርድ ቢሰጠኛ የገንዘብ ቅጣት፣ እርስ፣ ወይም ሁለቱንም ሊያጋጥመኝ እንደሚችል እገነዘባለሁ።

________________________ ________________
*በቁጥጥር ስር የገባ ሰው ፊርማ* *ቀን*

### ☐ ተመላሽ የማይሆን ገንዘብ ከፍሎ መለቀቅ (ፖስት ኤንድ ፎርፈይቸር) ብቻ

**ክስ፡ ______________________ተመላሽ የማይደረግ የሚከፈል ገንዘብ መጠን፡** $

የተከፈለው (ገንዘብ) እንደማይመለስልኝ በማወቅ በክስ(ሶች) የተወሰነው ለመክፈል ወስኛለሁኝ። እንደማይመለስልኝ በማወቅ በክስ(ሶች) የተወሰነው በመክፈሌ በፍርድ ቤት ችሎት የመቅረብ መብቴ እየተውኩኝ እንደሆነ ይገባኛል።

________________________ ________________
*በቁጥጥር ስር የገባ ሰው ፊርማ* *ቀን*

**በኮቪድ ምክኒያት ሊደረግ የሚችል ማስተካከያ**

**የፍርድ ቤት ቀጠሮዎ ተለዋጭ ቀጠሮ የተሰተበት ከሆነ አዲሱ ቀንዎ በwww.tinvurl.com/dc-citations ያግኙ**

### ☐ ፍርድ ቤት ባዘዘው ቦንድ መለቀቅ ብቻ (ኮርት ኦርደርድ ቦንድ ረሊዝ ኦንሊ)

*ኦፊሰሮች፡ እባክዎ በቁጥጥር ስር ያለው የዲ.ሲ. ሲፒርየር ዳኛ ባስተላለፈው የእስር ማዘዣ መሰረት ቦንድ የከፈለ ከሆነ ይህን ያጠናቅቁ*

ቁጥጥር ስር ውስጥ የገቡት በወንጀል ጉዳይ በፍርድ ቤት ቀጠሮዎ ባለመገኘትዎ ምክኒያት የዲ.ሲ. ሲፒርየር ዳኛ ባስተላለፈው የእስር ማዘዣ መሰረት ነው። ከታች በተጠቀሰው ቀንና ሰአት ፍርድ ቤት ቁጥር C-10, የ500 Indiana Ave., NW, Washington, D.C. ሪፖርት ማድረግ ይኖርብዎታል:

____________ በ 9:30 ኤ.ኤም.
**ቀን** **ሰአት**

**የቦንድ መጠን**
$

ቦንድ እየከፈለ ያለ ሰው ስምና አድራሻ

________________
**ስም**

________________
**አድራሻ**

ፍርድ ቤቱ የወሰነው የቦንድ መጠን ከፍያለሁ። ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰአት እንደምቀርብ ቃል እገባለሁ። ፍርድ ቤት ባልቀርብ እንድታሰር የሚያዝ የፍርድ ቤት ማዘዣ (ቤንች ዋራንት) ሊተላለፍብኝ እንደሚችል ይገባኛል። በተጨማሪ ፍርድ ቤት ሳልቀርብ ብቀር በወንጀል ጥፋት ተከስሼ ፍርድ ቤት ባለመቅረብ ወንጀለኛ ነህ የሚል ፍርድ ቢሰጠኛ የገንዘብ ቅጣት፣ እርስ፣ ወይም ሁለቱንም ሊያጋጥመኝ እንደሚችል ይገባኛል።

________________________ ________________
*በቁጥጥር ስር የገባ ሰው ፊርማ* *ቀን*

### ☐ ቁጥጥር ስር የገባ ሰው መገኛ መረጃ

ጠበቃ የመያዝ መብት፡ ፍርድ ቤት የመደበው ነጻ ጠበቃ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የተመደበልዎ ጠበቃ ያገኝዎት ዘንድ ይህን ክፍል በግልጽ ይሙሉ።

**ቴሌፎን፡** ________________________________

**ኢመይል፡** ________________________________

**አድራሻ፡** ______________________ **አፓርታማ፡** ____

**ከተማ/ስቴት/ዚፕ፡** ____________________________

### ☐ ቁጥጥር ስር ለማስገባት የተሰጠ ማስታወቂያ መቀበሌ ማረጋገጫ

ቁጥጥር ስር ለማስገባት የተሰጠ ማስታወቂያ መቀበሌንና ማንበቤን፣ መብቶቼም እንደተረዳሁኝ አረጋግጣለሁ።

________________________ ________________
*በቁጥጥር ስር የገባ ሰው ፊርማ* *ቀን*

በአደጋ ጊዜ ተጠሪ ስም፡ ____________________________

በአደጋ ጊዜ ተጠሪ ቴሌፎን፡ ____________________________

በዲስትሪክት ሲፒርየር ፍርድ ቤት አክቲንግ ክለርክ (ጸሀፊ) የተሰጠ

________________________ ____________ ____________
*የስቴሽን ክለርክ (ጸሀፊ) ፊርማ* *የባጅ ቁጥር* *ዩኒት*

# በቁጥጥር ስር ለገቡ ሰዎች የሚሰጥ ማስታወቂያ (ኖቲስ ቱ አረስትድ ፐርሰንስ)

*መለቀቅዎንና ግዴታዎን የሚያብራራ ከታች ያለውን መረጃ ይመልከቱ። ከታች ያለው መረጃ ማስታወቂያ በቅድሚያ ሳይሰጥ ሊቀየር ይችላል።*

## ☐ እስር ቤት ሳይገቡ መለቀቅ (ሳይቴሽን ረሊዝ)

ብቁ ከሆኑ፣ በዚህ ሰነድ (እስር ቤት ሳይገቡ መለቀቅ (ሳይቴሽን ረሊዝ) ክፍል) በገጽ 1 በሰፈረው **ቀንና ሰአት** ወደ ዲ.ሲ. ሲፒርየር ፍርድ ቤት 500 Indiana Ave., NW, Washington, D.C. እሄዳለሁ በማለት በሚሰጡት ቃል ወዲያውኑ ሊለቀቁ ይችላሉ።

በሰሩት ጥፋት መሰረት የወንጀል ክስ ፋይል እንደሚደረግና እንደማይደረግ አቃቤ ህግ (ፕሮሰኪቶር) ይወስናል። ፍርድ ቤት ባይቀርቡ እንዲታሰሩ የሚያዝ የፍርድ ቤት ማዘዣ (ቤንች ዋራንት) ሊተላለፍ ይችላል። ጉዳይዎ መሰረዙ የሚያመለክት ማረጋገጫ ካገኙ ፍርድ ቤት መቅረብ የለብዎትም።

እስር ቤት ሳይገቡ ሲለቀቁ (ሳይቴሽን ረሊዝ) እንደ ቅድመ ሁኔታ ፍርድ ቤት እስኪቀርቡ ድረስ ከተወሰነ/ኑ ሰው/ሰዎች እንዳይገናኙ እና እንዲርቁ፣ ወይም ከተወሰኑ ቦታ እንዲርቁ መመሪያ ሊሰጥዎ ይችላል።

ከሰው/ቦታ ይርቁ ዘንድ የተሰጠው ትእዛዝ ከጣሱ የፖሊስ ኦፊሰር ወዲያውኑ ቁጥጥር ስር ውስጥ ሊያስገቡዎ ይችላል፣ ፍርድ ቤቱ በሚከፈትበት በሚቀጥለው ቀን ፍርድ ቤት ይቀርባሉ። አቃቤ ህጉ ወንጀል በመፈጸም የከሰስዎ ከሆነ በጠበቃ የመወከል መብት ይኖርዎታል። ጠበቃ መቅጠር የማይችሉ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ጠበቃ ይመድብሎታል።

**አስፈላጊ መረጃ**

ምንም እንኳን ቁጥጥር ስር ውስጥ የገቡ ቢሆኑም መንግስት በፍርድ ቤት ክስ ፋይል ላያደርግ ይችላል። የእምነት ክህደት ቃል ለመስጠት (አረይንመንት) በሚመጡበት ቀን እስር ቤት ሳይገቡ የተለቀቁበትን ቅጽ ይዘው ወደ ፍርድ ቤት መምጣት አስፈላጊ ነው፣ ምክኒያቱም መንግስት እርስዎን በፍርድ ቤት መክሰሱንና አለመክሰሱን ለመለየት ሊያስፈልግዎ የሚችል መረጃ ያለው ስለ ሆነ ነው።

**የመዝገብ መረጃ (ኬዝ ኢንፎርሜሽን) ለማግኘት**

መዝገብዎ ያለበት ሁኔታ በተመለከተ መረጃ ቢፈልጉ የዲ.ሲ.ፍርድ ቤት ወንጀለኛ ክፍል የደምበኞች አገልግሎት መስመር **(202)879-1373** መደወል ይችላሉ።

## ☐ በቦንድ መለቀቅ (ቦንድ ረሊዝ)

ቁጥጥር ስር ውስጥ የገቡት የፍርድ ቤት ትእዛዝ ባለማክበርዎ ይታሰሩ ዘንድ በተላለፈ ትእዛዝ (ቤንች ዋራንት) መሰረት ነው። የእስር ትእዛዙ ያስተላለፈው ዳኛ የወሰነው ቦንድ መጠን መክፈል ይችላሉ። ቦንዱን ከከፈሉ በዚህ ሰነድ በገጽ 1 በተጠቀሰው **ቀንና ሰአት** ፍርድ ቤት ለመቅረብ በሚሰጡት ቃል ይለቀቃሉ። እንዲቀርቡ በተነገርዎ ቀንና ሰአት ባይቀርቡ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ባለማክበር እንዲታሰሩ የሚያዝዝ ሌላ የእስር ትእዛዝ ሊተለለፍ ይችላል። ምንም እንኳን አቃቤ ህጉ ጉዳዩ ለመሰረዝ ቢወስንም ፍርድ ቤት ባለመቅረብዎ ሊከሰሱ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ በተመደበልዎ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ባይቀርቡ የከፈሉት የቦንድ ገንዘብ ሊያጡ ይችላሉ።

## ☐ *ተመላሽ የማይደረግ ገንዘብ ከፍሎ ለመለቀቅ የሚሆን ገንዘብ (ፖስት ኤንድ ፎርፈይት ማኒ)*

*ተመላሽ የማይደረግ ገንዘብ በመክፈል ለመለቀቅ ብቁ በሆነ ጥፋት የተከሰሱ ከሆንና ተመላሽ የማይደረግ ገንዘብ ከፍለው ለመለቀቅ ብቁ ከሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ ለጥፋቱ የወሰነውን የገንዘብ መጠን ቢከፍሉ ጉዳዩ ያልቃል። የተመደበው ገንዘብ ለመክፈል ቢመርጡ የከፈሉት ገንዘብ ተመላሽ **አይሆንም**፣ ምክኒያቱም እየተከፈለ ያለው ገንዘብ ተመላሽ አይሁን ብለው እየተስማሙ ስለ ሆነ። ተመላሽ የማይደረግ ገንዘብ ከፍለው ቢለቀቁ ቀጥሎ ሊያጋጥም በሚችል የወንጀል፣ የፍትሐብሔር፣ ወይም የአስተዳደር የፍርድ ቤት ሂደት ወይም እርምጃ ማንኛውም የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍርድ ቤት ወይም ኤጀንሲ ማንኛውም ማእቀብ፣ ቅጣት፣ ከፍ ያለ ፍርድ (ኢንህንስድ ሰንተንስ)፣ ወይም የፍትሐብሔር አካል ጉዳት አይጣልም። ቁጥጥር ስር ገብተው እንደነበረ በመዝገብ (ሬከርድ) **ይኖራል**። ቁጥጥር ስር ውስጥ መግባትዎ ታትሞ እንዳይታይ (ሲል እንዲደረግ) ከፈለጉ በሱፒርየር ፍርድ ቤት አቤቱታ ፋይል ማድረግ ይችላሉ። ጉዳይዎም ታትሞ እንዳይታይ (ሲል) ማድረግ በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ቢፈልጉ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፓብሊክ ዲፈንደር ሰርቪስ (የህዝብ ተከላካይ አገልግሎት) በ**202-628-1200** ወይም በኢመይል [www.pds.dc.org](http://www.pds.dc.org) ማግኘት ይችላሉ።*

- ***ሀሳብዎ ቢቀይሩና ክሶችዎ ለመከራከር ቢወስኑስ?*** *ገንዘብዎ ከከፈሉ በኋላ ፍርድ ቤት መቅረብ ቢፈልጉ "ከፍሎ መገላገል የሚለውን መሳብ እፈልጋለሁ የሚል አቤቱታ (ሞሽን ቱ ሰት አሳይድ ፎርፈይቸር)" ከዛሬ ቀን ጀምሮ ባሉ 90 ቀናት ውስጥ ፋይል ማድረግ ይችላሉ።*
- ***መንግስት ተመላሽ የማይደረግ ገንዘብ ከፍለው መለቀቅዎ ለመቃወም ቢወስንስ?*** *የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ቢሮ፣ የዚህ ጉዳይ አቃቤ ህግ፣ በ90 ቀናት ውስጥ "ከፍሎ መገላገል የሚለውን መሳብ እፈልጋለሁ የሚል አቤቱታ (ሞሽን ቱ ሰት አሳይድ ፎርፈይቸር)" ፋይል ማድረግ ይችላል።*
- ***ፍርድ ቤቱ አቤቱታው ቢፈቅደውስ?*** *የእርስዎ ወይም የመንግስት አቤቱታ ቢፈቀድ ክሶቹ እንደገና እንዲመለሱ ይደረጋል፣ እርስዎም ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ይኖርብዎታል ማለት ነው። ጠበቃ የመቅጠር አቅም የሌለዎት ከሆነ ፍርድ ቤት ለሚመድበው ጠበቃ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።*

*ተመላሽ የማይደረግ ገንዘብ ከፍለው ለመለቀቅ ካልመረጡና የወንጀል ጉዳይዎን ለመከራከር ከመረጡ  እስር ቤት ሳይገቡ ለመለቀቅ (ረሊዝ ኦን ሳይቴሽን) ብቁ ይሆናሉ።*

## ☐ በትራፊክ ጥፋቶች ቁጥጥር ስር ውስጥ ለገቡ ሰዎች የሚሆን ጠቃሚ ማስታወቂያ

***መንጃ ፈቃድ ስለሌልዎ (ኖ ፐርሚት)*****፣ ከእገድ በኋላ በመንዳትዎ** ወይም **ከስረዛ በኋላ በመንዳትዎ** ምክኒያት ቁጥጥር ስር ውስጥ የገቡ ከሆነ የሚከተሉትን ሰነዶች በፍርድ ቤት ቀጠሮዎ ይዘው ቢመጡ ጉዳይዎን ፈጥነው እንዲፈቱ ሊረዳዎት ይችላል፡

- ***ያለ መንጃ ፈቃድ (ኖ ፐርሚት)*****፡** ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ዲፓርትመንት ኦፍ ሞቶር ቨሂክልስ (ዲ.ኤም.ቪ.) የተሰጠ ትክክለኛ መንጃ ፈቃድ (ወይም የመንጃ ፈቃድ መማሪያ ፈቃድ) ወይም ትክክለኛ ከዲሲ-ውጪ በሌላ ስቴት (አውት-ኦፍ-ስቴት) ፈቃድ **እና**  የ15-አመት የመንዳት መዝገብ (ድራይቪንግ ሬከርድ)።
- **ከእገድ ወይም ከስረዛ በኋላ መንዳት (ኦፐሬቲንግ አፍተር ሳስፐንሽን ኦር ሪቮኬሽን)፡** *መንጃ ፈቃድዎ የታገደ ወይም የተሰረዘ ከነበረ ከዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ዲፓርትመንት ኦፍ ሞቶር ቨሂክልስ ወይም ከስቴትዎ ዲፓርትመንት ኦፍ ሞቶር ቨሂክልስ ያልተከፈሉ የነበሩ ቲኬቶች ወይም የድጋፍ ሀላፊነቶች መከፈላቸው የሚያሳይ፣ እና መንጃ ፈቃድዎ እንደገና እንዲሰራ የማድረጊያ ክፍያዎች (ሪኢንስቴትመንት ፊስ) ጨምሮ መንጃ ፈቃድዎ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ ያደረጉ ችግሮች ማስተካከልዎ የሚያሳዩ ሰርቲፋይድ የሆኑ ሰነዶች ያቅርቡ። ሰነዶቹ በተጨማሪ መንጃ ፈቃድዎ ዳግም እንደሚሰራና (ሪኢንስቴትድ መሆኑ) በጥሩ አቋም ላይ መሆንዎን ማሳየት ይኖርባቸዋል።*